
Saturday, 31 January 2015 13:19

# የመምህሬ ወልደ ዮሐንስ ቀልዶችና አሽሙሮች




Written by ከጉማራ ዙምራ

- የዘንድሮ ህዳር አክሱም ጽዮን ዓመታዊ ክብረ በዓል ላይ የታደምኩት በመንፈሳዊ ጉዞ ታቅፌ ወይም ተደራጅቼ ሳይሆን ከስራዬ ጋር በተፈጠረልኝ መገጣጠም ነበር፡፡ እኔም እድሌን እያመሰገንኩ ዓመት በአሉን ታድሜ አመሻሽ ላይ ሻይ ቡና ለማለት ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ደመቅመቅ ወዳለችው አክሱም ከተማ ጎራ ብለን በአንድ ካፌ በረንዳ ላይ ስናወጋ፣ አንድ መጽሀፍ አዟሪ ሽፋኑ ላይ በእድሜ የገፉ አዛውንት የስላቅ ፈገግታ እያሳዩ የተነሱትን ፎቶ የያዘ የትግርኛ መጽሀፍ እንካችሁ አለን፡፡ እኔም “ቀልድታትን አሽሙራትን ምህረይ ወሊሃንስ” የሚለውን መጽሀፍ ገዝቼ እንደዋዛማገንበብጀመርኩ።
መጽሀፉ፤ መምሬ ወልደ ዮሃንስ ወልደ አብዝጊ የተባሉ አክሱም ውስጥ “እብዱ ሰው” በሚል ቅጽል ስም ሲጠሩ በዕድሜ ዘመናቸው የተናገሯቸው፤ የቀለዷቸውና ያሽሞሯቸውን ንግግሮች የያዘ ሲሆን (ሰው ባትም እንደ አለቃ ገብረሃና ሰፊ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያጠነጠኑ ናቸው) በሰለሞን ገ/ህይወት ተዘጋጅቶ በ 2006 ዓ.ም ለንባብ የበቃ መፅሃፍ ነው፡፡ የዚህ ጽሁፍ ዓላማ በመጽሀፉ ዙሪያ ሙያዊ ሂስ ለማቅረብ ሳይሆን በመጽሀፉ መግቢያ ላይ የተጻፈውን እጅግ ልብ የሚነካና አሳዛኝ የመምሬ ወልደ ዩሃንስ አጠቃላይ የህይወት ውጣ ውረድ ለማስቃኘት እንዲሁም ከመጽሀፉ ውስጥ አንባቢ ቢሰማቸው ብዬ ያመንኩባቸውን የተወሰኑ ዋዛና ቁምነገሮችን ማካፈል ነው፡፡ በተጨማሪም አዘጋጁ ይህን መጽሃፍ ወደ አማርኛ ተርጉሞ ለሌሎች አንባብያን እንዲደርስ ወንድማዊ ምክሬን ለመለገስ በማሰቤምጭምርነው። ወደ ታሪኩ ስንገባ ታዲያ!
ምህረይ ወልደ ዩሃንስ ወልደ አብዝጊ፤ ህዳር 3 ቀን 1917 ዓ.ም በአክሱም ዞን ናእዴር አዴት በተባለ ወረዳ፣ ጎዲቖ በተባለ ቀበሌ ውስጥ ተወለዱ የሚለን ጸሀፊው፤ በመቀጠልም እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ እስከ ጎጃም ድረስ በመሄድ ጥልቅ የቤተክህነት ትምህርት ተከታትለው በመምጣት በአዴት መድኀኒዓለም ቤተክርስቲያን ሲቀድሱ መኖራቸውን ይነግረናል።
እኚህ አዋቂ ሰው ትዳር መስርተው ሶስት ልጆችን ወልደው፣ እንደ ማንኛውም የገጠር አርሶ አደር ኑሯቸውን በግብርና ላይ መስርተው ሲኖሩ በነበረበት ወቅት፣ በ 1951 ዓ.ም በትግራይ “ዘመነ አንበጣ” እየተባለ የሚታወቀው የአንበጣ ወረርሽኝ በአዝመራው ላይ የነበረውን ቡቃያ አዝርእት በማጥቃት እንኳንስ ለሰው ልጅ ለከብቶች እንኳን ገለባ ሳይተው እንዳልነበረ አደረገው፡፡ በዚህ ጊዜም ምህረይ ወልደ ዩሀንስ እንዲህ አሉ ይባላል፤ “አቤቱ ጌታዬ! መቼም የአንተ ፍጥረት ሆነን አንበጣን ለምን ፈጠርክ አንልም፡፡ አንበጣስ ቢሆን የአንተው ፍጥረት አይደል? ከሆነልህ አንበጦቹን ወደ ንብ ቀይርልንና ማር እንኳን ቢሰጡን። አምላኬ!! ለኛ ቀርቶ ለከብቶቻችን የሚሆን ገለባ እንኳን ሳያስቀሩ አንበጦቹ ቅርጥፍጥፍ አድርገው ሲያወድሙት መቼስ ምን እንበል?” አሉ ይባላል፡፡ ይህ ሁኔታ ግን የምህረይ ህይወትን የሚቀይር ክስተት አስከትሎ መጣ ይለናል ጸሐፊው፡፡ ምን አስከተለ? የሚል ጥያቄ ማንሳት መቼም ተገቢ ነው፡፡
ነገሩ ወዲህ ነው፡፡ ከአንበጣ መንጋው አደጋ በኋላም ምህረይ ይቀድሱበት በነበረው ቤተክርስቲያን ቅዳሴው ተጠናቆ ገድለ እዮብን አንብበው እንዲህ አሉ፤ “ተመስገን ነው የሚባለው ጎበዝ? ተመስገን በሉ፡፡ እዮብ ያ ሁሉ መከራ ወርዶበት ተመስገን ነው ያለው፡፡ ተመስገን በማለቱም አምላክ ዳግም ፈጠረው፡፡ የሆነው ሆኖ ፈጣሪ ተመስገን ነው የሚፈልገውና ተመስገን በሉ፡፡” በወቅቱ በቤተክርስቲያን የሚካሄደው ምህላ ከወትሮው የተለየ ነበር፡፡ ህጻን አዋቂ፤ አሮጊት ሽማግሌ ሳይቀር በጉልበቱ ተንበርክኮ ምህላ ለእግዚአብሔር ያቀርባል። ይህን የታዘቡት ምህረይም፤

“እናንተ ሰዎች ይህን ምህላ ለአባቶቻችንና ለእናቶቻችን እንተውላቸው፡፡ እናንተ ወጣቶች ግን እስኪ አምላክን እናግዘው፡፡ ስደት እንሂድና ችግሩን እናሳልፍ፡፡ በጓዳ ያለውን እህል እየቆሉ በልተውም ቢሆን እድሜያቸውን ቢገፉ ትተልናቸው እንሂድ። አምላክ ጸሎታችንንና ምህላችንን ቢሰማ እንኳን ዝናብ እንጂ ገብስ አያዘንብልንም፡፡ በዚህ በጋ ወቅት ዝናብ ቢያዘንብ እንኳን ችለው የሚጠመዱ በሬዎች የሉንም፡፡” ብለው አቅም ያላቸውንና እንችላለን የሚሉ ሰዎችን ጨምረው ስደት ሆነ፡፡ ወዴት? ተስፋ ወደ አሳደሩበት ፀለምት፡፡ ሸቅለውም ሆነ ለምነው የቤተሰቦቻቸውን እስትንፋስ ለማራዘም ትንሽዬ መኮትኮቻቸውን ይዘው በመንገድ ከገበሬ በቤት እየለመኑ፤ ስር እየማሱና እየተመገቡ መሪሩን የበረሃ ጉዞ ያለ በቂ እህልና ውሃ ተያያዙት፡፡ ያ የበረሃ ጉዞ ግን እንደታሰበው ቀላል አልነበረም፡፡ ሁለቱን ልጆቻቸውን የትኩሳት ህመም አሸነፋቸውና እጅ ሰጡ፡፡ የአንዱን ልጅ ስም ጠርተው አልቅሰው ሳያበቁ ሁለተኛው ልጅ ተከተለ፡፡
ግማሽ እድሜያቸውን እያወደሱና እየቀደሱ ያገለገሉትን ፈጣሪ ቀና ብለው ተማጸኑ፡፡ ከወሰደ የማይመልስ ፈጣሪ ግን ምላሽ አልሰጠም፡፡ ዝም! በቃ ዝም! አምላክ እንደ እዮብ ሊፈትነኝ ሳይሆን አይቀርም ብለው የሚወዷት ሚስታቸውንና አንድ ልጃቸውን እየተመለከቱ፤ “ተመስገን እንጂ ሌላ ምን ይባላል አምላኬ?” አሉ፡፡ ይህን የሰሙ ሚስታቸው “ምን አሉ?” ሲሏቸው “ተመስገን ነው ያልኩት” ሲሉ ሚስትየው አከታትለው አጓሩ፡፡ “ሆይ … ሆይ” በማለት፡፡

ምህረይ ሁለቱን ልጆቻቸውን ቀብረው እንደ ሰማይ ኮከብ የራቀችው ጸለመት ላይ ለመድረስ በዚያ በበርሃ ዳዴ ሆነ፡፡ ዳዴ ብቻ፡፡ የሰሜን ምዕራብ የትግራይ በረሃን እየወደቁ እየተነሱ መጓዝ ሆነ ምርጫው፡፡ የባለቤታቸው ጉልበት በሃዘንና በረሃብ መላወስ እያቃተው ሙክክ ብሎ ቀረ፡፡ ግንባራቸው በላብ ተጠምቆ፣ በረሃብና በውሃ ጥም የደረቀ ጉሮሮአቸውን ሊያረጥቡ ፈለጉ መሰለኝ “ውሃ፤ ውሃ፤ ው…ሃ እባክህ ውሃ ስጠኝ” እያሉ ማንቋረር ጀመሩ፡፡ የውሃ ጠብታ በሌለበት በረሃ ውሃ እያሉ፣ ውሃ ሆነው የልጆቻቸውን ዱካ ተከትለው አሸለቡ፡፡ ምህረይ ወልደ ዩሀንስ ምን ይበሉ? ምንስ ሊሉ ይችላሉ? ጸለምት ገብተው የሰዎችን እርሻ ኮትኩተው የቤተሰቦቻቸውን እስትንፋስ ለማትረፍ የያዟት መቆፈሪያ የሁለት ልጆቻቸውና የባለቤታቸው ጉድጓድ መቆፈሪ ሆነች፡፡ በቃ ወደ ሰማይ አንጋጠው ፈጣሪን ተመለከቱ፡፡ እልህ ይሁን ብስጭት ባሸነፈው አንደበት “አልክ!? አልክ አይደለም? ካልክስ ደስ ይበልህ! ተመስገን!” አሉ፡፡ በእጃቸው የያዙትን መቆፈሪያ “አሁንስ ማን ቀረሽ ይሆን?” ብለው አርቀው አሽቀንጥረው ወረወሯት፡፡ የተረፈ አንድ ልጃቸውን ይዘው፣ ቁጣ ጉልበት አበደራቸው መሰለኝ፣ ከሩጫ በማይተናነስ እርምጃ ከሚስታቸው መቃብር ሽሽት ሆነ፡፡ ከሞት ሽሽት!!
ልጃቸውን አዝለው ከፊት ለፊታቸው የተገተረውን ተራራ መቧጠጡን ተያያዙት። አሰጋገራቸው የተራራው ጫፍ ላይ ወጥተው ፈጣሪን ሊሟገቱ ይመስላል፡፡ ተራራው ጫፍ ላይ ሳይደርሱ ግን ጀምበር አዘቀዘቀች፡፡ ታዲያ ይህ ሁኔታ በፈጠረላቸው አጋጣሚ ከተራራው ወገብ ላይ በሩቁ በገዳመ ጰንጠልዮን የመነኑ ባህታውያን የያዙት እሳት ብልጭ ብልጭ ሲል ታያቸው፡፡ ተመስገንን ዘንግተው የነበሩት ምህረይ፣ በዚያች የእሳት ብልጭታ ምክንያት ተመስገንን አስታውሰው፤ “ተመስገን… ተመስገን… ተመስገን .. አምላኬ” አሉ፡፡ መጾም መጸለይ ሰርክ ተግባራቸው የሆነው ምህረይ፣ እንኮኮ አድርገው ላዘሉት ልጃቸው አንዳች የሚበላ ነገር አቅምሰው እድሜውን ማራዘም ነበረባቸው፡፡ እንደ ዝንጀሮ በአራት እግራቸው ተራራውን እየቧጠጡ ገዳሙ ጋር ሲደርሱ፣ እንደርሳቸው ስደት የወጡ ወጣቶች የተጋገረ ቂጣ ሲበሉ አገኟቸው፡፡ ቂጣው እንዳያልቅ የሰጉት ምህረይ፣ ያለ ቀልባቸው “እባካችሁ ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ ለልጄ የሚሆን ትንሽ አስተርፉልኝ” እያሉ መማጸናቸውን ያዙ፡፡ አንድ ባህታዊ ቀበል አድርገው “ይበሉ እንጂ ጌታዬ የሚበላ ሞልቷል ይልቅ ለጁን ያውርዱትና እህል አቅምሱት” ሲሏቸው ድንግጥ ብለው “ተመስገን … ተመስገን … ጌታዬ!” ብለው ልጃቸውን ከጀርባቸው ላይ ዳሰስ ቢያደርጉት እስትንፋስ አልቦ ሆኖ ድርቅ ብሏል፡፡ ለዘላለም አንቀላፍቷል፡፡ ምህረይ ከዚህ በኋላ ፈጣሪን ተመስገን ይበሉት ይውቀሱት የሚያስታውሱት ነገር የለም፡፡ ይሁን እንጂ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሊገቡባት አስበዋት የነበረችው ጸለምት ከተማ ለብቻቸው ገብተው “እኚህ ወፈፍ የሚያደርጋቸው ሰውዬ መጡ” እያለ የከተማው ህዝብ ይናገር እንደነበር ብቻ ነው የሚያስታውሱት፡፡

ከረጅም ጊዜ በኋላ ዘመን ሲቀየር እብድ እየተባልኩ ጸለምት ከምኖር ወደ ሚያከብረኝ ህዝብ ሄጄ የቤተሰቤን ማለቅ አርድቼ፣ ደብሬን እያገለገልኩ ብኖር ይሻለኛል ብለው ወደ ትውልድ ቀዬአቸው ተመለሱ፡፡ ወደ ቀዬአቸው ሲገቡ ግን ያዩት ነገር አስደንጋጭ ሆነ፡፡ መኖሪያ ቤታቸው ፈርሶ፣ በማሽላና በጤፍ አዝርእት ተሸፍኖ፣ የአንድ ቤተሰብ አባላት አጨዳ ሲያካሂዱ አገኟቸው፡፡ በውስጣቸው “እውነትም ሰው እንደሚለው ሳላብድ አልቀረሁም?” ብለው አንዲት ቃል ግን ሳይተነፍሱ አረፍ አሉ፡፡ በወቅቱ አዴት ከተማ ውስጥ እዳጋ ሰሉስ በሚባል ቦታ መሬታቸውን የወሰደው ሰው ከሹመኛ ዳኛ ጋር እየተሳሳቀ ሲያወራ ያገኙትና ሞግተው እንደማይረቱት ተገንዝበው አማራጭ ስላልነበራቸው፣ ወደ ፍርድ ቤቱ ሰሌንና አነስተኛ እራፊ አቡጀዲ ለብሰው ቀረቡ፡፡ ዳኛው ተገርሞ፤ “ምህረይ ለምንድን ነው ሰሌን ለብሰው የመጡት?” ብሎ ይጠይቃቸዋል፡፡ ምህረይም ተስፋ በቆረጠ አንደበት፤ “ሞቴ ካልቀረ ብትገንዙኝ ብዬ ነው የመጣሁት” ሲሉ ችሎቱ በሳቅ ተሞላ፡፡ ቀጠለ፡፡ ምህረይም “ከእንግዲህ የተረፈኝ ምህረይ! እንዲህ አሉ የሚል ተረት ብቻ እንጂ ፍትህ አላገኝም” ብለው ወደ ጎዳና ወጡ፡ አክሱም ከተማ ከሃውልቱ ስር እንዲሁም በሽሬ ጎዳናዎች ላይ ብርድና ጸሃይ ሲፈራረቁባቸው ኡኡታቸውን ማሰማት ቀጠሉ፡፡ ሰዎች ከመሬት ተነስተው የሚጮሁ እየመሰላቸው አበዱ ሲሏቸው መሳቅ፤ መዝፈንና ማፏጨት እለታዊ ተግባራቸው ሆነ፡፡ ምህረይ ወልደ ዩሃንስ “እብድ” የሚል ተቀጽላ ስም ተሰጥቷቸው፣ እርሳቸውም እብድነታቸውን በጸጋ ተቀብለው አዝናኝና አሽሟሪ ንግግራቸውን ለሰው እያካፈሉ መኖር ጀመሩ፡፡ በጣም የሚገርመው የታሪካቸው ክፍል ደግሞ ቀን እብድ እየተባሉ ከተማ ውስጥ ሲዞሩ ውለው ለሊት በቤተክርስቲያን ቆመው ጸሎት ሲያደርጉ ማደራቸው ነበር፡፡ ወደ ሞታቸው አቅራቢያ ወዳጆቻቸው በቆርቆሮ ቤት ሰርተው፣ ልብሳቸውንም ቀይረውላቸው ያኖሯቸው ነበር፡፡ በዚያች ቆርቆሮ ቤት ውስጥ ለአንድ ዓመት ከስምንት ወር ተቀምጠው፣ እግራቸው ላይ በወጣች ቁስል ምክንያት ህመም በርትቶባቸው ህዳር 28 ቀን 1998 ዓ.ም በ 81 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ የእኚህን ታላቅ ሰው ቅኝት ከመቋጨቴ በፊት ለዛሬ አንድ ሁለት የተናገሯቸውን አሽሙሮች ላካፍላችሁ፡፡

ማበድ መልካም

ምህረይ ወልደ ዩሃንስ ብዙ ጊዜ ወደ ፍርድ ቤት እየሄዱ ወንጀለኞች የፈጸሟቸውን የወንጀል ተግባራት ሲሰሙ ይውሉ ነበር፡፡ ታዲያ ባንዱ ቀን አንድ ጤነኛ ተብሎ የሚታመን ሰው የፈጸመው ወንጀል በጣም አስገርሟቸው ነው መሰለኝ በመንገድ ላይ “ማበድ መልካም!! ማበድ መልካም!! ማበድ መልካም!!” እያሉ ከተማዋን ሲዞሩ ዋሉ፡፡

ሁኔታቸው የገረመው አንድ ሰው አስቆማቸውና፤ “ምህረይ፤ እንዴት ብሎ ነው ማበድ መልካም የሚሆነው? ምን እያሉ ነው?” ብሎ ሲጠይቃቸው፤ “አብደህ እየው ልጄ!! አብደህ እየው ልጄ! አብጄ ነው መልካም መሆኑን የተረዳሁት” ብለውት አለፉ።

“ለኔ ብለው”

ምህረይ አክሱም ማሪያም ቤተክርስቲያንን እየሳሙ ሳለ አንድ አራጣ አበዳሪ ያዩና፤ “እስኪ ብር ይስጡኝ?” ይሏቸዋል፡፡ እኚህ አራጣ አበዳሪ ታዲያ ቆጣ ብለው “ዛሬ ማሪያም አይደለችም እንዴ! ስለማሪያም ብለው ይለምኑና እንስጥዎት፡፡ ምንድን ነው እንዳስቀመጡት ገንዘብ ብር ስጡኝ ማለት!!” ይሏቸዋል፡፡

ምህረይ ወልደ ዩሃንስ ቀበል አድርገው፡- “አቤት … አቤት … መጽደቂያ ሊያደርጉኝ ፈልገው ነው? ከፈለጉ ለኔ ብለው ይስጡኝ፡፡ ካልፈቀዱ ደግሞ ይቅርብኝ፡፡” ብለዋቸው ሄደ፡፡ (አራጣ አበዳሪ አይጸድቅም ስለሚባል)

“እኩልነት”

ምህረይ ወልደ ዩሃንስ የሚወዱትን ቢራ ተጋብዘው እየጠጡ እያለ፣ አንድ ታጋይ ቀረብ ይልና እንዲህ ይላቸዋል፡-

ታጋዩ፡- “ምህረይ፤ አሁን ነው ድሮ የጾታ እኩልነት የተረጋገጠው?”

ምህረይ - “ድሮ ነበር እንጂ እኩልነት የነበረው፤ አሁን የታለ” ይሉታል፡፡

ታጋዩ ተገርሞ፡- “እንዴት?” ይላቸዋል፡፡

ምህረይ ቀበል አድርገው፤ “ዛሬማ ወንዶች ለብቻችን እየተገረዝን ምን እኩልነት አለ ብለህ ነው?” አሉት ይባላል፡፡